https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፱
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 69
ADDIS ABABA, 27th May, 2019

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፪ /፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ማቋቋሚያ (እንደተሻሻለ) አዋጅ.....፲፩ሺ፪፻፷፯

CONTENT

Proclamation No. 1142/2019

The Ethiopian Institution of the Ombudsman Establishment(As Amended)Proclamation….....Page 11266

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፪ /፪ሺ፲፩

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት የመንግስት አሰራር ለህዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን እንዳለበትና የመንግስት ባለስልጣን ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ እንደሚሆን በመመልከቱ፤

የመንግስት አስፈጻሚ አካላት የሚያከናውኗቸው ተግባራት ከዜጎች የዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር ያላቸው ቁርኝት ከመብታቸው ጋር በተሳሰረ ሁኔታ የሚኖራቸው የወሳኝነት ሥልጣን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ በመምጣቱና የአስፈጻሚ አካላት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከህገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎች ወሰን ውጪ ያላለፈ መሆኑን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

የአስተዳደር በደል እንዳይፈጸም አስቀድሞ በመከላከል ወይም ተፈጽሞ ሲገኝ በአፋጣኝ እንዲታረም በማድረግ በሀገራችን የመልካም የአስተዳደር ሥርዓትን ለመገንባት የሚደረገው ጥረት ስኬታማ የሚሆነው ተቋማዊ የአሠራር

PROCLAMATION NO. 1142/2019

A PROCLAMATION TO AMEND ETHIOPIAN INSTITUTION OF AMBUDSMAN ESTABLISHMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it is provided in the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia the conduct of affairs of the Government shall be transparent and that any Public Official shall be accountable for failure in Official Duties;

WHEREAS, the interlinkage of the activities, and of Decision-Making Powers of Executive Organs of Government with the daily lives and the rights of citizens is an ever-increasing and widening circumstance and it is necessary to make sure that Executive organs act within constitutional parameters;

AWARE THAT, a Free and Independent Institution of Ombudsman with high Institutional and Functional Autonomy plays an indispensable role in the National endeavor building order of Good Governance in Ethiopia;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

https://chilot.me

ነጻነቱ የተረጋገጠ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ሲኖር መሆኑን በመረዳት፤

በአስፈጻሚ አካላት የሚፈጸሙ የአስተዳደር በደሎች ወይም የሕግ ጥሰቶች እንዲታረሙ በተቋሙ የሚሰጥ የመፍትሔ ሐሳብ ለማስፈጸም መሰናክል የነበረን ክፍተት በማስወገድ በምርመራ እና ቁጥጥር ሥራዎቻችን ያዳበርናቸውን አዎንታዊና ገንቢ ልምዶች የመጠበቅንና ይበልጥ የማጠናከርን አስፈላጊነት በማመን፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፭) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩፻፩፻፶፪ /፪፻፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **"ምክር ቤት"** ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማለት ነው፡፡

፪/ **"ተጠሚ"** ማለት በምክር ቤት የሚሾም ዋና ዕንባ ጠባቂን፣ ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂ፣ የሴቶች፣ የህፃናት፣ የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን ዕንባ ጠባቂ እና የቅርንጫፍ ዕንባ ጠባቂ ነው፡፡

፫/ **"ተቋም"** ማለት የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ማለት ነው፡፡

COGNIZANT OF, the necessity of preserving and consolidating past achievements and positive practices pertaining to awareness creation, supervision and investigation while removing legal impediments that hinder executing remedies provided by the Ethiopian Institution of Ombudsman,

NOW,THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (15) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia; it is hereby proclaimed as follows:

PART ONE
GENERAL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "The Ethiopian Institution of the Ombudsman Establishment (Amendment)Proclamation No. 1142/2019″

2. Definitions

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1/ **"House"** means the House of People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

2/ **"Appointee"** means the Chief Ombudsman or the Deputy Chief Ombudsman or Women, Children, Persons with Disability and Elders Ombudsman and the branch Ombudsman, appointed by the House, in accordance with this Proclamation.

3/″ **Institution"** means the Ethiopian Institution of the Ombudsman.

https://chilot.me

፬/ **"የአስተዳደር በደል"** ማለት ስልጣን ባለዉ አካል የወጣ እና በስራ ላይ ያለን ሕግን በመፃረር በመንግስት አስፈፃሚ አካላት ወይም በመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚፈፀም ድርጊት ወይም የሚሰጥ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ማለት ሲሆን የተሰጠን ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ አለመፈጸምን ይጨምራል፡፡

4/ **"Maladministration"** includes acts committed , decisions given or failure to give decision, omission by Executive Organs or Public Development Enterprise,in contravening applicable laws related to Administration.

፭/ **"ሕግ"** ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት፣ የክልል መንግስታት ህገ መንግስት እና በፌደራል ወይም በክልል መንግስታት የሚወጡ ህጎች ማለት ነው፡፡

5/ **"Law"** include the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, the Constitution of a Regions as well as Federal or Regional Laws and Regulations.

፮/ **"መንግስት"** ማለት የፌደራል ወይም የክልል መንግስት ማለት ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡

6/ **"Government"** mean Federal or Regional Government and include Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations.

፯/ **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፵፯(፩) ላይ የተመለከቱት ማለት ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡

7/ **"Region"** means any of those specified under Article 47 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and, for the purpose of this Proclamation, includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations.

፰/ **"የመንግስት መስሪያ ቤት"** ማለት ሚኒስቴር፣ ኮሚሽን፣ ባለስልጣን፣ ኤጀንሲ፣ ኢንስቲቱት ወይም ማናቸውም ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ነው፡፡

8/ **"Government Office"** means Ministry, Commission, Authority, Agency, Institute or any Government Office.

፱/ **"የመንግስት የልማት ድርጅት"** ማለት በመንግስት ባለቤትነት ስር የሚገኝ የማምረቻ፣ የማከፋፈያ፣ አገልግሎት ሰጭ ወይም ሌላ አይነት ድርጅት ነው፡፡

9/ **"Public Enterprise"** means a Production, Distribution, Service-rendering or other Enterprise, under the ownership of the Government;

https://chilot.me

፲/ **"አስፈፃሚ አካል"** ማለት የመንግስት መስሪያ ቤትን ወይም የመንግስት የልማት ድርጅትን እንዲሁም በዳኝነት ሰጭ ወይም በህግ አውጪው አካል ውስጥ የአስተዳደር ወይም የአስተዳደር ነክ አገልግሎት የሚሰጥ አካልን ይጨምራል፡፡

10/ **"Executive Organ"** includes Government Office or Public Enterprise as well as Organs rendering Administrative or related Services within the Judiciary or the Legislature;

፲፩/ **"ባለስልጣን"** ማለት የሕዝብ ተመራጭ ወይም የመንግስት አስፈጻሚ አካል ተሿሚ ወይም ኃላፊ ነው፡፡

11/ **"Official"** mean an Elected Representative or an Appointee or Official of an Executive Government organ.

፲፪/ **"ሠራተኛ"** ማለት የተቋሙ ዳይሬክተሮችን፣ የዋና ዕንባ ጠባቂ ጽ/ቤት ኃላፊን፣ ቡድን መሪዎች፣ ባለሙያዎችንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ይጨምራል፡፡

12/ **"Staff"** mean Employees of the Institution, which includes Directors, Head of Chief Ombudsman Office, Team Leaders,professionals and support staff of the Institution.

፲፫/ **"መርማሪ"** ማለት የምርመራ ስራ እንዲያካሂድ በዋና ዕንባ ጠባቂው ወይም በቅርንጫፍ ዕህፉት ቤት ደረጃ ደግሞ በቅርንጫፍ ዕንባ ጠባቂው የተመደበ ሰራተኛ ነው፡፡

13/ **"Investigator"** means a staff assigned, by Chief Ombudsman or at the Branch Level by Branch Office Ombudsman to conduct an investigation on Maladministration.

፲፬/ **"ስልታዊ ምርመራ"** ማለት በመንግስት የአስተዳደር መዋቅር ምደባ፣ አሰራርና ሌሎችም ላይ የተከሰቱ የአስተዳደር ችግሮችን የሚመለከቱ ሲሆን በባህሪያቸዉ በበርካታ የህብረተሰብ ክፍል ላይ ጉዳት ሊያከትል በሚችል ጉዳዮች ላይ የሚካሄድ ምርመራ ማለት ነው፡፡

14/ **"Systemic Investigation"** means the process of examining a Maladministration concerning Government Administration structure assignment, conduct and others that will affect a group of people by their nature.

፲፭/ **"ቤተ ዘመድ"** ማለት በክልል የቤተሰብ ህግ ወይም በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ መሰረት የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ሰው ነው፡፡

15/ "Family Member" means a person related to each other by Consanguinity or Affinity, in accordance with the Federal and Regional Family laws.

፲፮/ **"ሶስተኛ ወገን"** ማለት ቤተዘመድ ወይም በህግ አግባብ ውክልና የተሰጠው ወይም አንድን ቡድን የሚወክል የህዝብ ተመራጭ ወይም ማህበር ወይም የመብት ተሟጋች ድርጅቶች ወይም ማንኛውም ሰው ነው፡፡

16/ **"Third party"** means Family Member or a Legal Representative or a person who is elected to represent a group or association or Organization working on Civil Right Advocacy or any person.

https://chilot.me

፲፯/ **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

17/ **"Person"** means any Natural or Juridical person;

፫. ስለ ፆታ አገላለፅ

በዚህ አዋጅ በወንድ ፆታ የተደነገገው ለሴት ፆታም ያገለግላል፡፡

3. Gender Expression

Provisions of this Proclamation set out in the Masculine Gender shall also apply to the Feminine Gender.

፬. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በየደረጃው በሚገኙ የመንግስት አስፈፃሚ አካላት በሚፈፀሙ የአስተዳደር በደሎችና ባለስልጣኖች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

4. Scope of Application

This Proclamation shall apply to maladministration committed by the Executive Organs, and Officials thereof, of a Government.

ክፍል ሁለት
ስለኢትዮጵያ የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

PART TWO
ABOUT ETHIOPIAN INSTITUTION OF OMBUDSMAN

፭. የማቋቋሚያ አዋጁን ስለማሻሻል

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም (ከዚህ በኋላ "ተቋሙ" እየተባለ የሚጠራ) በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) እና (፲፭) በተደነገገው መሠረት የሕግ ሰውነት ያለው ሆኖ ራሱን ችሎ በዚህ አዋጅ ተሻሽሎ ተቋቁሟል፡፡

5. Amending the Establishment Proclamation

The Ethiopian Institution of the Ombudsman (hereinafter referred to as "The Institution") is hereby established as amended by this Proclamation in accordance with Article 55 (1) and (15) of the Constitution of Federal Democratic Republic of Ethiopia as an autonomous Organ having its own Juridical personality.

፩/ የተቋሙ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ ጉባኤዉ በአገሪቱ በማናቸውም ቦታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ለመክፈት ሲፈልግ ለምክር ቤቱ አቅርቦ ያፀድቃል፡፡

1/ The Institution shall have its Head Office in Addis Ababa, and when the council needs to open branch offices at any place with in the country it shall submit its proposal to the House for approval.

፮. ዓላማ

የተቋሙ ዓላማ በሕግ የተደነገጉ የሰዎች መብቶች እና ጥቅሞች በአስፈፃሚው አካላት መከበራቸውን በማረጋገጥ፣ የሕግ የበላይነትን መሠረት ያደረገ ጥራት፣ ቅልጥፍናና ግልጽነት ያለው መልካም የመንግሥት አስተዳደር እንዲሰፍን ማድረግ ይሆናል፡፡

6. Objective of the Institution

The objective of the Institution shall be bringing about Good Governance that is of High Quality, Efficient and Transparent based on the rule of law, by way of ensuring that People's Rights and Benefits, provided for by a law are respected by Organs of the Executive.

https://chilot.me

፯. <u>ስለ ተቋሙ ሥልጣንና ተግባር</u>

ተቋሙ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ አስፈፃሚ አካላት የሚያወጧቸው አስተዳደራዊ መመሪያዎች፣ የሚሰጧቸው ውሳኔዎችና አሠራሮቻቸው ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች እንዲሁም ሌሎች ህጎችን የማይቃረኑ መሆናቸውን የመቆጣጠር፤

፪/ የቀረቡለትን የአስተዳደር በደል አቤቱታዎች መሰረት በማድረግ ወይም በራስ ተነሳሽነት ወይም በአስፈላጊ ጉዳዮች ላይ ስልታዊ ምርመራ የማካሄድ፤

፫/ አስተዳደራዊ በደል መፈፀሙን ሲያረጋግጥ ተገቢዉን የመፍትሄ ሃሳብ የማቅረብ፤

፬/ አስፈፃሚው አካል ሥራውን በህግ መሰረት የሚያከናውን መሆኑን ለማረጋገጥና አስተዳደራዊ በደሎች እንዳይፈፀሙ ለመከላከል ቁጥጥር የማድረግ፤

፭/ አስተዳደራዊ በደሎች የሚቀረፉበትን ሁኔታ የማጥናትና ምክረ ሀሳብ የማቅረብ፤

፮/ የተሻለ የመንግስት አስተዳደርን ለማስገኘት ነባር ሕጎች ወይም አሰራሮች ወይም መመሪያዎች እንዲሻሻሉ፣አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ ወይም ፖሊሲዎች እንዲቀየሱ የማሳሰብ፤

፯/ በመልካም የመንግስት አስተዳደር ጉዳዩች ላይ ለመንግስት የምክር አገልግሎት የመስጠት፤

፰/ ሕብረተሰቡ ስለመልካም አስተዳደር እና ስለ አስተዳደራዊ ፍትህ ግንዛቤ እንዲኖረው የተለየዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ግንዛቤ የመፍጠር፤

፱/ በዓለም አቀፍ የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች በሚመለከት ስብሰባዎች ኮንፍረንሶች ሲምፖዚየም ላይ መሳተፍ፤

7. <u>Power and Function of the Institution</u>

The Institution shall have the following power and functions:

1/ To supervise Regulations or Administrative Directives that issued by Executive Organs or decisions given by Executive Organs and the practices thereof do not contravene the Constitutional Rights of Citizens and a Law as well;

2/ To conduct investigation on the basis of complaints submitted or on its own initiation on Maladministration or conduct Systemic Investigation on important issues;

3/ To recommend appropriate remedies where it believes that Maladministration has occurred;

4/ Conduct supervision, with a view to ensuring that the Executive carries out its functions in accordance with the law and to prevent Maladministration;

5/ Undertake studies and finding solutions to take actions on Maladministration and give Recommendation;

6/ Make Recommendations for the revision of existing Laws, Practices or Directives and for the enactment of new Laws and formulation of Policies, with a view to bringing about Good Governance;

7/ Provide advice to the Government on the issue of Good Governance;

8/ Create awareness of Good Governance and on matters related to Administrative Justice;

9/ Participate in International Good-governance related meetings or conferences or symposium;

https://chilot.me

፲/ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት ህግ ክፍል ሶስት ተግባራዊ ስለመደረጉ መከታተልና የመቆጣጠር፤

፲፩/ ዓላማዉን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን::

10/ Supervise and follow up implementation of part three of Freedom of Mass Media and Access to Information Law;

11/ Perform such other related activities as required for the attainment of its Objectives.

፰. <u>የተቋሙ ተጠሪነት</u>

የተቋሙ ተጠሪነት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል።።

8. <u>Accountability of the Institution</u>

The Institution shall be accountable to the House of People's Representatives.

፱. <u>የሥልጣን ገደብ</u>

ተቋሙ የሚከተሉትን ጉዳዩች የመመርመር ሥልጣን የለዉም ፡-

፩/ በሕዝብ ምርጫ የተቋቋሙ ምክር ቤቶች በሕግ አውጭነታቸው የሚሰጧቸው ውሳኔዎችን፤

፪/ በፍርድ ቤቶች ወይም በህግ የመዳኘት ስልጣን በተሰጣቸው አካላት በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዩች ወይም የታዩና ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዩችን፤

፫/ በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም በክልል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በመታየት ላይ ያሉ እና የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን፤ወይም

፬/ በመከላከያ ሠራዊትና በፖሊስ ክፍሎች የሚሰጡ የፀጥታ ወይም የሀገር መከላከል ጉዳዮችን በሚመለከት የሚሰጡ ውሳኔዎችን ።።

9. **<u>Limitation of Power</u>**

The Institution shall have no power to investigate the following issues:

1/ Decision given by councils, established by election, in their legislative capacity;

2/ Decision given or cases pending in courts of law or quasi- judicial organs;

3/ Decision given or cases pending on matters under investigation by the Federal or Regional Office of the Auditor-General; or

4/ Decision given by police Forces or Defense Forces, in respect of matters of National Security or Defense.

<u>ክፍል ሶስት</u>
<u>የተቋሙ አቋም፣ ሥልጣንና ተግባር</u>

<u>PART THREE</u>
<u>ORGANIZATION OF THE INSTITUTION, POWER AND FUNCTION</u>

፲. <u>የተቋሙ አቋም</u>

ተቋሙ፡-

፩/ የዕንባ ጠባቂ ጉባኤ ፤

፪/ አንድ ዋና ዕንባ ጠባቂ፤

፫/ አንድ ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂ፤

፬/ አንድ የሴቶች፣ የሕጻናት፣ አካል ጉዳኞች እና አረጋውያን ዕንባ ጠባቂ፤

10. <u>Organization of the Institution</u>

The Institution shall have:

1/ Council of the Ombudsman;

2/ A Chief Ombudsman;

3/ A Deputy Chief Ombudsman;

4/ An Ombudsman heading the women, children, persons with disability and Elders;

https://chilot.me

፫/ የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዕንባ ጠባቂ እና

፮/ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይሆናል፡፡

፲፩. <u>የተቋሙ ጉባኤ</u>

፩/ የተቋሙ ዕንባ ጠባቂዎች ጉባዔ (ከዚህ በኋላ "ጉባዔ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፣

፪/ ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ዋና ዕንባ ጠባቂ .....ሰብሳቢ

ለ) ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂ.....ምክትል ሰብሳቢ

ሐ) የሴቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ዕንባ ጠባቂ.....አባል

መ) የቅርንጫፍ ዕንባ ጠባቂዎች.....አባል

፫/ ጉባዔው የራሱን ፀሐፊ ከአባላቱ መካከል ይመርጣል፣

፬/ ጉባዔው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፪. <u>የጉባዔው ሥልጣንና ተግባር</u>

ጉባዔው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ይህን አዋጅ ሥራ ላይ ለማዋል መመሪያዎችን እና የውስጥ ደንቦችን የማፅደቅ፣

፪/ በተቋሙ ረቂቅ በጀት ላይ የመምከር፣

፫/ የመንግስት ሠራተኞች ሕግ ቢኖርም ጉባኤዉ፡-

ሀ) ለተቋሙ ስራ አመቺ የሆነ አደረጃጀትና መዋቅር አጥንቶ በስራ ላይ ያዉላል፣

5/ Branch office Ombudsman; and

6/ The necessary staff.

11. <u>Council of the Institution</u>

1/ Council of Ombudsmen (hereinafter referred to as "The Council") is hereby re-established.

2/ The Council shall have the following members:

a) Chief Ombudsman…….Chair person

b) Deputy Chief Ombudsman…Deputy Chair person

c) Women, children persons with disabilities and Elders Ombudsman……..……Member

d) Branch office Ombudsman…..…..…..Member

3/ The Council may elect its Secretary from Members of the Council.

4/ The Council may draw-up its own rules of procedure of meeting.

12. <u>Power and Function of the Council</u>

The Council shall have the following Power and Functions:

1/ Adopt Directives and Internal Regulations necessary for the implementation of this Proclamation;

2/ Discuss on draft Budget of the Institution;

3/ Notwithstanding the Federal Civil Servants Proclamation, the Council:

a) Undertake and implement organizational structure study as may be appropriate for its functions;

https://chilot.me

ለ) ለተቋሙ ሠራተኞች ልዩ የደመወዝና ስኬል ስርዓት አጥንቶ ለምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

ሐ) የተቋሙ ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን የአስተዳደር መመሪያ ያወጣል፤

መ) ለተቋሙ ሠራተኞች የጥቅማ ጥቅም ክፍያ አስመልክቶ አጥንቶ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

፬/ የተቋሙን ዳይሬክተሮች የመመደብ፤

፭/ የዳይሬክተሮችን የዲሲፕሊን ጉዳይ መርምሮ ዉሳኔ መስጠት፣

፮/ የሚቀርቡለትን የሰራተኛ አስተዳደር ጉዳዮች ወይም አቤቱታዎች መርምሮ ውሳኔ የመስጠት::

፲፫. <u>የዋና ዕንባ ጠባቂው ሥልጣንና ተግባር</u>

፩/ ዋናው ዕንባ ጠባቂ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ሆኖ የተቋሙ የበላይ ኃላፊ በመሆን በዚህ አዋጅ ለተቋሙ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ዕንባ ጠባቂ፤

ሀ) የተቋሙ ዕንባ ጠባቂዎች ጉባዔ በሚያጸድቀው መመሪያ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል ፣ ያስተዳድራል፤

ለ) በተቋሙ ዕንባ ጠባቂዎች ጉባኤ የተመከረበት ረቂቅ በጀት አዘጋጅቶ በቀጥታ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

b) Shall study a special salary scale of the Employees and submit the study to the House and implement the same up on approval;

c) Issue Administration Directive for the Administration the Staff of the Institution;

d) Undertake study concerning the staff benefit Package and submit it to the House.

4/ Assign Directors of the Institution;

5/ Investigate and Decide on disciplinary cases relating to Directors;

6/ Investigate and render a final decision on cases, petitions or complaints submitted to it in relation to Staff Administration;

13. <u>Power and Function of Chief Ombudsman</u>

1/ The Chief Ombudsman shall be accountable to the house and the superior head of the Institution and, as such, shall exercise the Power and Functions of the Institution provided for under this Proclamation.

2/ without prejudice to the generality stated under sub-Article (1) of this Article, the Chief Ombudsman shall:

a) Employ and administer the staff, in accordance with the Directive to be adopted by the Council.

b) Prepare draft Budget which is consulted by the Council, directly submit to the House and implement same upon approval;

https://chilot.me

ሐ) በቂ ምክንያት ሲኖረው አንድ ጉዳይ ከአንድ የምርመራ ክፍል ወይም መርማሪ ወደ ሌላ የምርመራ ክፍል ወይም መርማሪ ያዛውራል፤ወይም በራሱ ይመረምራል፤

መ) ተደጋጋሚ የአስተዳደር በደሎችን አጥንቶ ከመፍትሔ ሀሳብ ጋር ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤

ሠ) አስተዳደራዊ ጉዳዩችን የሚመለከቱ ረቂቅ ህጎችን አዘጋጅቶ ያቀርባል፤ በሌሎች አካላት በተዘጋጁ ላይ አስተያየት ይሰጣል፤

ረ) አስተዳደራዊ በደሎችንና የተቋሙን የስራ አካሂድ አስመልክቶ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፤

ሰ) ተቋሙን በመወከል በስብሰባዎች ይካፈላል፣ከፌደራሉና ከክልል መንግስታት አካላት እንዲሁም መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የስራ ግንኙነት ያደርጋል፤

ሸ) ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ቀ) በምክር ቤቱ የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

፫/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፪ ፊደል ተራ (ለ፣ሠ፣ እና ረ) እና በአንቀፅ ፵፪ ከተጠቀሱት በስተቀር ሌሎች ጉዳዮችን በሚመለከት ዋና ዕንባ ጠባቂው ለተቋሙ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለዕንባ ጠባቂዎች ወይም ለሌሎች ኃላፊዎች ወይም ሌሎች ሰራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

c) Transfer a case, where he has sufficient grounds, from one investigation section or investigator to another or, himself, investigate a case of Maladministration occurring any where;

d) Undertake study of recurrent cases of Maladministration and forward together with remedial proposals to the House;

e) Prepare and submit Draft Administrative Legislations, give his opinion on those prepared otherwise;

f) Submit a report to the House on matters of Maladministration and on the activities of the Institution;

g) Take part in meetings by way of representing the Institution, establish working relations with Federal and Regional Government organs as well as with Non-Governmental Organizations;

h) Organize,coordinate, follow up and monitor the activities of branch offices;

i) Undertake such other activities as are assigned to him by the House.

3/ The chief ombudsman may, to the extent necessary for the efficient performance of the Institution, delegate part of his powers and duties, other than those specified under sub-Article (2) (b, e and f) of this Article and under Article 42, to Ombudsmen or to other staff members of the Institution.

https://chilot.me

፲፬. የምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂው ተጠሪነቱ ለዋና ዕንባ ጠባቂ ሆኖ የተቋሙን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት እና በማስተባበር ዋና ዕንባ ጠባቂውን ይረዳል፡፡

፪/ ዋና ዕንባ ጠባቂው በማይኖርበት ጊዜ ለዋና ዕንባ ጠባቂው የተሰጡትን ስራዎች ያከናውናል፡፡

፫/ በዋና ዕንባ ጠባቂው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

14. Power and Function of the Deputy Chief Ombudsman

1/ The Deputy Chief Ombudsman shall be accountable to the chief Ombudsman and shall Assist the Chief Ombudsman in Planning, Organizing, Directing and Coordinating the activities of the Institution.

2/ Undertake the activities of the Chief Ombudsman, in the absence of the latter.

3/ Carry out such other activities as may be assigned to him by the Chief Ombudsman.

፲፭. የሴቶች፣ የሕጻናት፣ አካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን ዕንባ ጠባቂ ሥልጣንና ተግባር

፩/ የሴቶች፣ የሕጻናት፣ አካል ጉዳተኞች እና የአረጋውያን ዕንባ ጠባቂ ተጠሪነቱ ለዋና ዕንባ ጠበቂ ሆኖ ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን የሚመለከቱ ተግባራትን በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት እና በማስተባበር ዋና ዕንባ ጠባቂውን ይረዳል፡፡

፪/ በዋናው ዕንባ ጠባቂዉ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

15. Power and Function of Women, Children, Persons with Disabilities And Elders Ombudsman

1/ Women, Children, Persons with Disabilities and Elders Ombudsman shall be accountable to the Chief Ombudsman and have the duties, Assist the Chief Ombudsman in Planning, Organizing, Directing and Coordinating activities concerning Women, Children, Persons with Disabilities and Elders.

2/ Carry out such other activities as may be assigned by the Chief Ombudsman.

፲፮. የቅርንጫፍ ዕንባ ጠባቂ ሥልጣንና ተግባር

የቅርንጫፍ ዕንባ ጠባቂው ተጠሪነቱ ለዋና ዕንባ ጠበቂ ሆኖ የቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቱ የበላይ ኃላፊ በመሆን በዚህ አዋጅ በአንቀፅ ፭(፩) በተቋቋመበት ስፍራ ውስጥ ለተቋሙ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ከማዋል በተጨማሪ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

16. Powers and Function of branch office Ombudsman

The Branch Ombudsman shall be accountable to the Chief Ombudsman and have the following Power and Function in addition to exercising, within the Local Jurisdiction of a Branch Office, the power and Function of the Institution specified under Article 5(1) of this Proclamation; an Ombudsman shall, as the Superior Head of a Branch Office, have the following Power and Functions:

https://chilot.me

፩/ የመንግስት አስተዳደር ሕጎች እና ሌሎች ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን የማረጋገጥ፤

፪/ በቂ ምክንያት ሲኖረው አንድ የአስተዳደር ጉዳይ ከአንድ የምርመራ ክፍል ወይም ከአንድ መርማሪ ወደ ሌላ የማዛወር ወይም ራሱ ምርመራ የማካሄድ፤

፫/ አስተዳደራዊ በደሎችን በተመለከተ ለዋና ዕንባ ጠባቂ ዝርዝር ሪፖርት የማቅረብ፤እንዲሁም በተቋቋመበት ስፍራ ለሚገኝ ክልል ምክር ቤት በጽሁፍ የማሳወቅ፤

፬/ ከመልካም አስተዳደር መርህ ጋር የማይጣጣሙ ህጎችና የአሰራር ልምዶች እንዲሻሻሉ ሐሳብ የማቅረብ፤

፭/ በተቋሙ ዕንባ ጠባቂዎች ጉባዔ በሚወጣዉ መመሪያ መሰረት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱን የመምራት፤

፮/ ለቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ በተፈቀደው በጀት መሰረት ክፍያዎችን የመፈጸም፤

፯/ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱን በመወከል ከክልል መንግስት አካላትና በተቋቋመበት ሥፍራ ውስጥ ከሚሰሩ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የስራ ግንኙነት የማድረግ፤

፰/ በዋና ዕንባ ጠባቂ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን፡፡

1/ To ensure that administrative and other laws, Regulations and Directives are observed;

2/ To transfer an Administrative Case from one investigation section or investigator to another or to conduct Investigation himself, where necessary;

3/ To submit detail report on matters of Maladministration to the Chief Ombudsman, and notify to the Council of the Region in written form;

4/ To forward proposals for the Revision of Laws and practices inconsistent with principles of Good Governance;

5/ To direct the Branch Office, in accordance with Directives issued from the Council of the Institution;

6/ To effect payments in accordance with the Budget allocated to the Branch Office;

7/ To establish working relations, as a representative of the branch office, with Regional Government Organs and Non-Governmental Organizations operating with in its Local Jurisdiction;

8/ To perform such other functions as are assigned to him by the Chief Ombudsman.

https://chilot.me

ክፍል አራት

ስለ ዕንባ ጠባቂዎች አሿሿምና መመዘኛዎች

፲፯. አሿሿም

፩/ የተቋሙ ተሿሚዎች በምክር ቤቱ ይሾማሉ።

፪/ የተቋሙ ተሿሚዎች አሿሿም የሚከተለው የአመራረጥ ሥርዓት ይኖረዋል።

ሀ) ተሿሚዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰ መሰረት በሚቋቋመው የዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ ይመለመላሉ።

ለ) ዕጩዎቹም በኮሚቴው ሁለት ሶስተኛ ድምፅ የተደገፉ መሆን አለባቸው።

ሐ) ዕጩዎቹ በምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔ አማካኝነት ለምክር ቤቱ ቀርበው ድምጽ የሚሰጥባቸው ይሆናል።

መ) የቀረቡት ዕጩዎች በምክር ቤቱ ሁለት ሶስተኛ ድምፅ ሲደገፉ ይሾማሉ።

፲፰. የዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ ጥንቅር

የዕጩ ተሿሚ አቅራቢ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩/ የምክር ቤቱ አፈጉባዔ…… ሰብሳቢ

፪/ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባዔ…… ……አባል

፫/ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የሚመረጡ አምስት አባላት…… አባል

፬/ በምክር ቤቱ መቀመጫ ካላቸው ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል በጋራ ስምምነት የሚመረጡ ሁለት የምክር ቤቱ አባላት ……አባል

PART FOUR

ETHIOPIAN INSTITUTION OF THE OMBUDSMAN APPOINTEES APPOINTMENT AND ITS CRITERIA

17. Appointment

1/ The Appointees of the Institution shall be appointed by the House.

2/ The appointment of the Appointees shall be made as under the following procedure:

a) The Appointees shall be recruited by a Nomination Committee to be formed pursuant to Article 18 of this Proclamation.

b) The Nominees shall have to receive the support of a two-thirds vote of the members of the Committee.

c) The list of Nominees shall be presented to the House, by the Speaker, for it to vote upon;

d) The Nominees shall be appointed upon receipt of a two-thirds vote of the House.

18. Composition of the Nomination Committee

The Nomination Committee shall have the following members:

1/ The Speaker of the House……..Chair person

2/ The Speaker of the House of Federation ……Member

3/ Five Members to be elected from Members of the House……..…Member

4/ Two members of the House to be elected by joint agreement of competent political parties having seats in the House……...…… Member

https://chilot.me

፫/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት.....አባል

5/ The President of the Federal Supreme Court.....Member

፲፱. <u>ለሹመት የሚያበቁ መመዘኛዎች</u>

ከዚህ በታች የተመለከቱትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ሰው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ሆኖ ሊሾም ይችላል፡-

19. <u>Criteria for Appointment</u>

Any person who fulfill the following crierias may be appointed as an Ombudsman:

፩/ ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ፤

1/ Is an Ethiopian National;

፪/ ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ተገዥ የሆነ፤

2/ Is loyal to the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

፫/ በህግ ወይም በአስተዳደር ወይም በተዛማጅ የትምህርት መስክ ከታወቀ ዩኒቨርስቲ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ እና በዘርፉ በቂ የስራ ልምድ ያለው፤

3/ Holds Degree in Law, Public Administration or other relevant discipline from recognized university with extensive work experience;

፬/ ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ገለልተኛ የሆነ

4/ Be Neutral from any Political Party;

፭/ በታታሪነቱ፣ በታማኝነቱ እና በሥነ-ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ፤

5/ Is Reputed for his Diligence, Honesty and Good Conduct;

፮/ ከደንብ መተላለፍ ውጪ በሌላ የወንጀል ጥፋት ተከሶ ያልተፈረደበት፤

6/ Has not been Convicted for a Criminal Offence other than Petty Offence;

፯/ ሥራውን ለመሥራት የሚያስችል ጤንነት ያለው፤ እና

7/ Be in a Good Health Condition to carry out his Duties; and

፰/ ዕድሜው ከ፴፭ ዓመት በላይ የሆነ።

8/ Is above thirty-five years of age.

፳. <u>የሥራ ዘመን</u>

20. <u>Term of the Office</u>

፩/ የተሿሚዎች የስራ ዘመን ስድስት ዓመት ይሆናል።

1/ The term of office of appointees shall be six years.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተዉ የስራ ዘመን ሲያበቃ ለአንድ ተጨማሪ ስድስት ዓመት ብቻ ሊሾሙ ይችላሉ።

2/ Up on expiry of the term of the Office specified under sub-Article (1) of this Article, the Appointees may be Re-Appointed only for one additional term.

https://chilot.me

፳፩. <u>የደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ክፍያ</u>

፩/ የተሿሚ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም የመንግስት ተሿሚዎች ጥቅማ ጥቅም ለመወሰን በወጣው ሕግ መሰረት ይፈጸማል፡፡

፪/ በአንቀጽ ፳፪ (፩) (ሀ፣ ለ፣ መ እና ሠ) መሰረት ሹመቱ ቀሪ የተደረገበት ወይም ከኃላፊነት የተነሳ ተሿሚ እንደገና ካልተሾመ በስተቀር ያገኘው የነበረውን ደሞዝና ጥቅማጥቅም በተመለከተ ሌሎች በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያሉ ተሿሚዎች በሚስተናገዱበት አሰራር የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

፳፪. <u>ተሿሚው ከኃላፊነት የሚነሳበት ምክንያት</u>

፩/ አንድ ተሿሚ በሚከተሉት ምክንያቶች ከኃላፊነት እንዲነሳ ወይም ሹመቱ ቀሪ እንዲሆን ሊደረግ ይችላል፡-

ሀ) ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለመልቀቅ ሲፈልግና አስቀድሞ የሦስት ወር ማስጠንቀቂያ በጽሑፍ ሲሰጥ፤ ወይም

ለ) በህመም ምክንያት ሥራውን በሚገባ ለማከናወን የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ወይም

ሐ) ሙስና መፈፀሙ ወይም ሕግን የሚጻረር ሌላ ድርጊት መፈጸሙ ሲረጋገጥ፤ ወይም

መ) ግልጽ የሆነ የሥራ ችሎታ ማነስ መኖሩ ሲረጋገጥ፤ ወይም

ሠ) የሥራ ዘመኑ ሲያበቃ ፡፡

21. <u>Payment of Salary and Benefits</u>

1/ the salary and other benefits of the appointees shall be determined in accordance with the law issued to provide for the benefits of government Appointees.

2/ An appointee discharged from responsibility or removed from Office, as per Article 22 (1) (a, b, d and e) unless re-appointed, issues concerning his salary and benefits will be Governed by the same procedure for those appointees of the same position.

22. <u>Grounds for Removal of an Appointee</u>

1/ An appointee may be removed from Office or discharged from responsibility upon the following circumstances:

a) Upon resignation, subject to a three-month prior written notice; or

b) where it is ascertained that he is incapable of properly discharging his Duties, due to Illness; or

c) where he is found to be Corrupted or to have committed other unlawful act; or

d) where it is ascertained that he is of manifest incompetence; or

e) Up on termination of his Term of Office.

፪/ አንድ ተሿሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ከኃላፊነት ከተነሳበት ወይም ሹመቱ ቀሪ ከሆነበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ በሌላ ተሿሚ መተካት ይኖርበታል፡፡

2/ With in three months of the removal or discharge of an appointee, as under sub-Article (1) of this Article, there shall be replaced another appointee shall be made to replace him.

፳፫. <u>ተሿሚው ከኃላፊነት የሚነሳበት ሥነ-ሥርዓት</u>

23. <u>Procedure for Removal of an Appointee</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ ፩ ከፊደል ተራ (ለ) እስከ (መ) በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሹመቱ ቀሪ እንዲሆን የሚደረገው ጉዳዩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፬ መሰረት በሚቋቋመው ልዩ አጣሪ ጉባኤ ከተመረመረ በኋላ ይሆናል፡፡

1/ An Appointee shall be removed from appointment, upon the grounds specified under Article 22 (1) (b – d) of this proclamation, subsequent to investigation of the matter by a Special Inquiry Tribunal to be formed as per Article 24 of this proclamation.

፪/ ምክር ቤቱ በልዩ አጣሪ ጉባዔው አብላጫ ድምጽ ተደግፎ የቀረበለት የውሳኔ ሀሳብ መርምሮ ሲያምንበት እና በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲደግፈው ተሿሚው ከኃላፊነት እንዲነሳ ይደረጋል፡፡

2/ An Appointee shall be removed from appointment, where the House finds that the recommendation submitted to it, as supported by the majority vote of the Special Inquiry Tribunal, is correct and where it upholds same by a two-thirds majority vote.

፳፬. <u>የልዩ አጣሪ ጉባዔው ጥንቅር</u>

24. <u>Composition of the Special Inquiry Tribunal</u>

ልዩ አጣሪ ጉባኤው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል ፡-

The Special Inquiry Tribunal shall have the following members:

፩/ የምክር ቤቱ ምክትል አፈ ጉባኤ…… ሰብሳቢ

1/ The Deputy Speaker of the House…Chair person

፪/ የፌደሬሽን ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ …… አባል

2/ The Deputy Speaker of House of Federation ……..Member

፫/ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የሚመረጡ ሦስት አባላት…… አባል

3/ Three Members to be elected from Members of the House ……..……..... Member

፬/ በምክር ቤቱ መቀመጫ ካላቸው ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ ስምምነት የሚመረጥ አንድ የምክር ቤቱ አባል ……አባል

4/ A Member of the House to be elected by joint agreement of competent Parties having seats in the House…… Member

፫/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ..... አባል

5/ Vice-President of the Federal Supreme Court……...…..…….……Member

፳፭. <u>በሌላ ሥራ መሰማራት ስለመከልከሉ</u>

25. <u>Prohibition to Engage in Other Employment</u>

፩/ ተሿሚው በሥራ ዘመኑ ክፍያን በሚያስገኝ በሌላ የመንግሥት ሆነ የግል ቅጥር ሥራ ላይ እንዲሰማራ አይፈቀድለትም ፡፡

1/ An appointee shall not be allowed to engage in other gainful, public or private employment during his term of Office.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ቢኖርም ተሿሚው አስተዋጽኦ እንዲያደርግ የሚፈለግበት የተለየ የሙያ መስክ ከግምት ውሰጥ ገብቶ በምክር ቤቱ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

2/ Notwithstanding the provisions of sub-Article (1) of this Article, the House may allow otherwise in consideration of the particular profession in which the appointee is required to make contribution.

<u>ክፍል አምስት</u>

PART FIVE

<u>የአቤቱታ አቀራረብና የምርመራ ሥነ-ሥርዓት</u>

<u>LODGING COMPLIANTS AND INVESTIGATION PROCEDURES</u>

፳፮. <u>አቤቱታ የማቅረብ መብት</u>

26. <u>The Right to Lodge Complaints</u>

፩/ አቤቱታ የሚቀርበው መብቱ ተጥሶብኛል በሚል ሰው ወይም በሶስተኛ ወገን ሊሆን ይችላል፡፡

1/ A complaint may be lodged by a person, claiming to have suffered from Maladministration or by a Third Party.

፪/ እንደተፈጸመው የአስተዳደር በደል ክብደት ተቋሙ የአመልካቹ ማንነት ሳይገልፅ የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች ሊቀበል ይችላል፡፡

2/ The Institution may, in consideration of the gravity of the Maladministration Committed, receive Anonymous Complaints.

፫/ ማንኛውም ሰው ለደረሰበት የአስተዳደር በደል ለተቋሙ አቤቱታ ከማቅረቡ በፊት አግባብነት ላላቸው አካላት ደረጃውን ጠብቆ ቅሬታውን የማቅረብ እና ውሳኔ ማግኘት ወይም በተወሰነው የጊዜ ገደብ ዉስጥ ውሳኔ ያላገኘ መሆን ይኖርበታል፡፡

3/Any person Prior to Lodging a Complaint to the Institution, in respect of an act of Maladministration from which he suffered shall be the one who submit his complaint before the relevant organs and get decision or unable to get decision with in a specified time .

፬/ በአንቀጽ ፱ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሰረት አቤቱታ የማቅረብ መብት በጉዳዩ የወንጀል ወይም የፍትሐብሄር ክስ መመስረትን አይከለክልም፡፡

4/ without prejudice to the provisions of Article 9 hereof, the right to lodge complaints, as under this Proclamation, shall be no bar to the institution of criminal or civil proceedings over the same case.

፫/ ተቋሙ አቤቱታዎችን ተቀብለው የሚመረምረው ያለምንም ክፍያ ነው፡፡

፳፯. ስለ አቤቱታ አቀራረብ

፩/ አቤቱታ በቃል ወይም በጽሁፍ ወይም በማንኛውም ሌላ መንገድ ለተቋሙ ሊቀርብ ይችላል፡፡

፪/ አቤቱታ በተቻለ መጠን ከደጋፊ ማስረጃዎች ጋር መቅረብ ይኖርበታል፡፡

፫/ አቤቱታ እንደሁኔታው በፌደራል ወይም በክልሉ የስራ ቋንቋ ሊቀርብ ይችላል፡፡

፳፰. ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ስለማድረግ

ተቋሙ አስፈላጊ ማጣሪያዎችን ለማካሄድ በቂ በሆነ ጊዜ ውስጥ ፡-

፩/ ተመርማሪዎች ለጥያቄ እንዲቀርቡ ወይም መልስ እንዲሰጡ፤

፪/ ምስክሮች ቀርበው ቃላቸውን እንዲሰጡ፤

፫/ ለጉዳዩ ጠቃሚ የሆነ ማስረጃ የያዘ ማንኛውም ሰው ይህንን ማስረጃ እንዲያቀርብ፤ ለማድረግ ይችላል፡፡

፳፱. መፍትሔ ስለመስጠት

፩/ ተቋሙ የቀረበለትን አቤቱታ በስምምነት ለመጨረስ የተቻለውን ሁሉ ማድርግ አለበት፡፡

፪/ የምርመራውን ውጤት ከነመፍትሔ ሀሳቡ ለሚመለከተው አካል የበላይ ኃላፊ በጽሁፍ ያቀርባል፡፡

፫/ ተቋሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት የሚሰጠው የመፍትሔ ሐሳብ ለተፈፀመው አስተዳደር በደል ምክንያት የሆነው ድርጊት ወይም አሰራር እንዲቆም ወይም ለበደሉ ምክንያት የሆነው መመሪያ

5/ The Institution shall receive and investigate complaints, free of any charge.

27. Lodging Complaints

1/ A Complaint may be lodged to the Institution orally, in writing or in any other manner.

2/ Complaint shall, to the extent possible, be submitted together with supporting evidence.

3/ Complaint may be made in Federal or Regional working language.

28. Ordering the Production of Evidence

In order to undertake necessary examination, within a reasonable time, the Institution may order that:

1/ Those complained against appear, at a specific time and place, for questioning or that they submit their defense;

2/ Witnesses appear, at a specific time and place, and give their testimony;

3/ Any person in possession of evidence, relevant to the case, produce same, at a specific time and place.

29. Remedies

1/ The Institution shall make all the effort it can summon to settle, amicably, a complaint brought before it.

2/ It shall notify, in writing, the findings of its investigation, and its remedies thereon, to the Superior Head of the concerned Organ.

3/ The remedy proposed by the Institution, pursuant to sub-Article (2) of this Article, shall expressly state that the act or practice having caused the Maladministration be discontinued or that the Directive having caused same be rendered

https://chilot.me

ተፈፃሚነቱ ቀሪ እንዲሆንና የተፈፀመው የአስተዳደር በደል እንዲታረም ወይም ተገቢ የሆነ ማንኛውም ሌላ እርምጃ እንዲወሰድ በግልፅ የሚያመለክት መሆን ይኖርበታል፡፡

፬/ ተቋሙ የምርመራ ዉጤቱን ለአቤቱታ አቅራቢዉ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፭/ ለተቋሙ የሚቀርቡ አቤቱታዎች ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ምላሽ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

4/ The Institutions shall inform complainant on the results of the investigation in writing

5/ Complaints submitted to the Institution shall be accorded not more than a period of six months.

፴. <u>የአስፈጻሚ አካላት ግዴታ</u>

30. <u>Duty of Executive Organs</u>

፩/ ተቋሙ አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች ወይም ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ወይም መልስ እንዲሰጡ ሲጠየቁ የተጠየቀው አካል በተሟላ አኳኋን የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

1/ Any individual, employees or officials up on request by investigator or appointee or any official of the Institution shall, forth with make relevant and necessary documents or response available which the investigator, appointee or any official of the Institution deemed it useful and necessary for investigation.

፪/ አስፈጻሚ አካላት በተቋሙ በቀረበ የምርመራ ውጤትና የመፍትሄ ሀሳብ ላይ በ፴ ቀናት ውስጥ የእርምት እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለበት፣ የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልተቻለ በቂ ምክንያት ካላቸዉ ይህንኑ በመግለፅ ለሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማሳወቅ ግዴታ አለባቸዉ፡፡

2/ The respondent are obliged to take corrective measures, within 30 days from the date of delivery, on findings and remedies sent to them by the Institution; if they are unable to take such measures, shall inform the same and the good reasons thereof to the Institution with in the specified period.

፴፩. <u>ይግባኝ የማቅረብ መብት</u>

31. <u>The Right to Appeal</u>

፩/ ማንኛውም አቤቱታ አቅራቢ ወይም አስፈጻሚ አካል የተቋሙ ኃላፊ ወይም መርማሪ በሰጠው የምርመራ ዉጤትና መፍትሔ ሀሳብ ወይም ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ከሆነ የምርመራ ውጤትና የመፍትሔ ሐሳብ ወይም ውሳኔዉ በጽሁፍ ከደረሰው ጊዜ አንስቶ በ፴ ቀናት ውስጥ በደረጃው

1/ Any compliant or Executive Organ that is aggrieved by the finding of investigation and remedy or decision of the Official of the Institute or investigator; has the right to submit his claim at all levels from the Director up to Chief Ombudsman with in 30 days from the time he is notified in writing of such finding of investigation and remedy or decision.Without

https://chilot.me

ከዳይሬክተር ጀምሮ እስከ ዋና እንባ ጠባቂው ቅሬታውን የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ሆኖ ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብና በመመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) መሰረት ቅሬታው የቀረበለት ተጀሚ ወይም ኃላፊ ወይም ዳይሬክተር የተሰጠውን የምርመራ ዉጤትና መፍትሔ ሐሳብ ወይም ዉሳኔ ማሻሻል፣ ማገድ፣ መሻር ወይም ማፅናት ይችላል።

፫/ ዋና ዕንባ ጠባቂው በ፴ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፤ የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል።

፴፪. <u>ቅጣት</u>

፩/ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) በተቋሙ መጥሪያ ደርሶት ወይም በሌላ ሁኔታ ተጠርቶ ካልቀረበ፤ ወይም

ለ) ለምርመራ ወይም ለቁጥጥር ስራ ማስረጃዎችን ወይም ሰነዶችን እንዲያቀረብ ተጠይቆ ተቋሙ በጠየቀው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማያቀርብ ፤ወይም

ሐ) የምርመራ ወይም የቁጥጥር ሥራ እንዳይሰራ እንቅፋት የሆነ፤ ወይም

መ) ምስክሮች ወይም አቤቱታ አቅራቢዎች ወይም ለተቋሙ ሥራ በማናቸውም መንገድ በተባበሩ ወገኖች ላይ ጥቃት ያደረሰ ፤ ወይም

ሠ) ያለ በቂ ምክንያት በተቋሙ በቀረበ የምርመራ ዉጤትና መፍትሄ ወይም የቁጥጥር ውጤት መሰረት የእርምት ዕርምጃ በ፴ ቀናት ውስጥ ያልወሰደ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ እስራት ወይም በብር

prejudice to this right of submitting a cliam; further implementation procedures shall be determined by Regulation and Directive.

2/ A Director or an Appointee who receives an objection, pursuant to sub-Article (1) of this Article, may Modify, Stay the Execution of, Reverse or Confirm the Finding of Investigation and Remedy or Decision having been proposed.

3/ The Chief Ombudsman shall give decision within 30 days and the decision shall be final.

32. <u>Penalty</u>

1/ Any person who;

a/ Has received summons from the Institution, or been called upon by it otherwise, does not appear; or

b/ Does not appear or respond to bring documents of investigation or supervision upon the request of the Institution ;or

c/ Obstructs the proper carrying out of the investigation or supervision of Institution; or

d/ Causes harm to Witnesses, Complainants or any person that cooperates by any means with the Institution; or

e/ Fails to take corrective measures, based on the findings of investigation and recommendation or findings of supervision of the Institution without good reasons, within 30 days; shall be punishable with imprisonment from five to seven years or

https://chilot.me

፲ ሺ(አስር ሺ ብር) የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሠ) የተዘረዘሩትን ጥፋቶች የፈጸመ ማንኛውም ሰው በሕግ እንዲጠየቅ ተቋሙ በቀጥታ ጉዳዩ ለሚመለከተው ዓቃቤ-ሕግ መስሪያ ቤት የድርጊቱን ሪፖርት ከደጋፊ ማስረጃዎች ጋር ያቀርባል፡ ከተቋሙ ትዕዛዝ የደረሰው ዓቃቤ ህግ መስሪያ ቤት አግባብ ባለው ሕግ መሰረት የወንጀል ክስ ይመሰርታል፡፡

2/ Any person who has Committed the Offences mentioned pursuant to this Article sub-Article 1 (a) to (e), shall be made accountable by law, the Institution shall report the case with supportive evidences to the concerned Attorney Office. The Attorney Office, upon, receiving order from the Institution, shall open Criminal suit rely on legal procedures.

፴፫. <u>የማሳወቅ ግዴታ</u>

ተቋሙ የምርመራ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ወንጀል ስለመፈፀሙ ያመነ እንደሆነ ለሚመለከተው አካል ወይም ኃላፊ ወዲያውኑ በጽሁፍ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

33. <u>Duty to Notify</u>

Where the Institution, in the process of conducting investigations believes that a crime is committed, it shall have the duty to, forthwith; notify same to the Concerned Organ or Official in writing.

፴፬. <u>የስልጣን መደራረብ</u>

፩/ በተቋሙና በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ሥልጣን ሥር የሚወድቁ ጉዳዮች በሚያጋጥሙ ጊዜ በማንኛቸው እንደሚመረመሩ በሁለቱ የጋራ ምክክር ይወሰናል፡፡

34. <u>Overlap of Jurisdiction</u>

1/ Where cases falling both under the jurisdiction of the Institution and of the Ethiopian Human Right Commission materialize, the question of which of them would investigate same shall be determined upon their mutual consultation.

፪/ አንድን ጉዳይ የትኛው አካል እንደሚመረመር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት መወሰን ካልተቻለ አስቀድሞ የቀረበለት አካል ይመረምራል፡፡

2/ Failing determination of the matter, as under sub-Article (1) of this Article, the organ having pendency shall undertake the investigation.

፴፭. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ተቋሙ ሥልጣንና ተግባሩን ሥራ ላይ ለማዋል እንዲችል ማንኛውም ሰው አስፈላጊውን ድጋፍ የመስጠትና የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

35. <u>Duty to Cooperate</u>

Any person shall provide the necessary assistance and duty to cooperate with a view to helping the Institution exercise its Power and Function.

https://chilot.me

፴፮. መግለጫ ስለመስጠት

፩/ ተቋሙ እንደአስፈላጊነቱ የምርመራ፣የቁጥጥር እና የጥናት ውጤቶችን አስመልክቶ በመገናኛ ብዙሀን ይፋዊ መግለጫ ይሰጣል፡፡

፪/ ተቋሙ መደበኛ ሪፖርትን ለምክር ቤት የማቅረብና አሰራሩን በሙሉ ለህዝብ ግልፅ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፫/ በተቋሙ የቀረበ የምርመራ ዉጤትና መፍትሄ ሀሳብ ለመፈፀም ተባባሪ ያልሆኑ አስፈጻሚ አካላት ዝርዝር በተመለከተ ልዩ ሪፖርት ለምክር ቤቱ ማቅረብ፣ ምክር ቤቱም ተገቢዉን እርምጃ ይወሰዳል፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (፩)፣ (፪) እና (፫) የተደነገገው ቢኖርም የአገሪቱ የፀጥታና ደህንነት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ለማድረግ ወይም የግለሰቦችን የግል ህይወት መብት ለመጠበቅ ሲባል በሚስጢር ሊያዙ በሚገባቸው ጉዳዩች ላይ ተቋሙ ጥንቃቄ የመውሰድ ግዴታ አለበት፡፡

36. Reporting

1/ The Institution shall issue an Official report on Investigation, Supervision and Research Findings through Mass Media as may be necessary.

2/ The Institution shall made its mode of operation transparent to the public and submit Regular Reports to the House.

3/ If the Executive Organ fails or refuses to implement the findings of investigation and recommendation of the Institution with in the specified time, the institution may prepare and submit to the House a special report detailing the failure or refusal to implement its recommendations and the House shall take appropriate action.

4/ Notwithstanding the provisions of sub-Article (1) ,(2) and (3) of this Article, the Institution shall have the duty to exercise caution in respect of matters to be kept secret, with a view to not endangering national security and well-being or to protecting individual lives.

፴፯. በስም ማጥፋት ስላለመጠየቅ

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረበ አቤቱታ በስም ማጥፋት አያስጠይቅም፡፡

፪/ ተቋሙ ስለሚያካሂደው ምርመራ ውጤት ለምክር ቤቱ የሚያቀርበው ሪፖርት ወይም በመገናኛ ብዙሃን በሚሰጠው ይፋዊ መግለጫ ወይም ሥራውን በማስመልከት በሚያደርገው ሌላ ዓይነት መግባፍ በስም ማጥፋት የሚያስጠይቅ አይሆንም፡፡

37. Non-Liability for Defamation

1/ No complaint lodged pursuant to this Proclamation shall entail liability for Defamation.

2/ No report of the Institution submitted to the House, on the findings of an investigation undertaken, nor any other correspondence of the Institution, relating to its activities, shall entail liability for Defamation

https://chilot.me

ክፍል ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፴፰. በጀት

፩/ የተቋሙ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል፡-

ሀ) በምክር ቤቱ በሚመደብ በጀት ፤

ለ) ከዕርዳታ፣ ከስጦታና ከማናቸውም ሌላ ምንጭ፡፡

፪/ ለተቋሙ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ የየሦስት ወሩ ድርሻ የሆነ የሥራ ማስኬጃ በቅድሚያ በሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ስም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ውስጥ በአንድ ጊዜ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

፴፱. የሂሣብ መዛግብት

፩/ ተቋሙ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የተቋሙ ሂሳብ በፌደራል ዋና ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

፵. ይግባኝ

፩/ ጉባኤው በሚሰጠው የአስተዳደር ውሳኔ ቅር የተሰኘ የተቋሙ ዳይሬክተር ውሳኔው ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በ፴ ቀናት ውስጥ የይግባኝ ቅሬታውን ለምክር ቤት አፈ ጉባኤ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

PART SIX

MISCELLANEOUS PROVISIONS

38. Budget

1/ The Budget of the Institution shall be drawn from the following sources:

a) Budget to be allocated by the House;

b) Assistance, grant and any other source.

2/ A proportionate quarterly appropriations of the operational Budget of approved Budget of the Institution shall be deposited in advance in the bank account opened in the name of the Institution.

39. Books of Accounts

1/ The Institution shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The accounts of the Institution shall be Audited annually, by Federal Auditor General.

40. Appeal

1/ Any Director of the Institution aggrieved by administrative decisions rendered by the Council may appeal to the Speaker of the House within 30 days from the date such decision has been made.

2/ Decisions rendered by the Speaker of the House pursuant to sub-Article (1) of this Article shall be final.

https://chilot.me

፵፩. በሌሎች ባለሙያዎች ስለመገልገል

ተቋሙ ለተለየ ሥራና ለተወሰነ ጊዜ ተገቢ የሆነውን ክፍያ በመፈፀም ለሥራ የሚያስፈልጉትን የራሱ ያልሆኑ ባለሙያዎችን መድቦ ሊያሠራ ይችላል፡፡

፵፪. ሚስጥር ስለመጠበቅ

በፍርድ ቤት ካልታዘዘ ወይም በዋና ዕንባ ጠባቂው ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም የተቋሙ ተሿሚ ወይም ሠራተኛ ወይም በአንቀጽ ፵፩ መሠረት የተመደበ ባለሙያ በሥራው አጋጣሚ ያወቀውን ምስጢር በማንኛውም ጊዜ የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

፵፫. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ ምክር ቤቱ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ጉባኤዉ ለዚህ አዋጅ እና ደንቦች አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፵፬. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በተቋሙ በምርመራ፣ በቁጥጥርና ጥናት ላይ የሚገኙ ጉዳዮች በቀድሞው ህግ መሠረት መታየታቸው ይቀጥላል፡፡

፵፭. የተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖረቸው ህጎች

፩/ የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋምን ለመቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፲፩/፲፱፻፺፪ በዚህ አዋጅ ተሸሯል፡፡

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተጠቀሱ ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

41. Utilization of Outside Professionals

The Institution may utilize, for a specific task and for a definite duration, outside professionals necessary for its functions, subject to making appropriate remunerations.

42. Observance of Secrecy

Unless ordered by a court or otherwise permitted by the Chief Ombudsman, any appointee or Professional employed pursuant to Article 41 of this Proclamation or staff or any other person shall have the obligation not to disclose, at all times, any secret known to him in connection with his duty.

43. Power to Issue Regulation and Directive

1/ The House may issue necessary Regulations for the implementation of this Proclamation.

2/ The Council may issue Directives for the implementation of this Proclamation and Regulation.

44. Transitory Provisions

Complaints on Maladministration that are under investigation by the Institution, prior to the enactment of this Proclamation, shall be investigated by the previous law of the Institution

45. Inapplicable Laws

1/ The Proclamation to established Ethiopian Institution of the Ombudsman Proclamation No, 211/2000 is here by repealed.

2/ No law or practice, inconsistent with this Proclamation, shall be applicable in respect of matters provided in this Proclamation.

https://chilot.me

፵፮. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

46. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 27th day of May 2019

SAHLEWORK ZEWDE

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA